ዳግሚት ፡ የሚል ፡ ነውና ፡ ቀዳማዊ ፡ አለ ፡ ተሰሎንቄ ፡ በመቄዶንያ ፡ ፊልጵስዩስና ፡ በአካይያ ፡ ቆሮንቶስ ፡ መካከል ፡ ያለች ፡ አገር ፡ ናት ፡ በአሬንጎና ፡ በይባባ ፡ መካከል ፡ ደራ ፡ እንዳለ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ከዚህ ፡ ገብቶ ፡ ጌታ ፡ ከፅንስ ፡ ጀምሮ ፡ ያደረገውን ፡ ተአምራት ፡ ያስተማረውን ፡ ትምህርት ፡ የመራውን ፡ ትሩፋት ፡ ቢነግራቸው ፡ አኩሎቹ ፡ አመኑ ፡ እኩሎቹ ፡ አናምንም ፡ አሉ ፡፡ ያላመኑት ፡ የሚጣሉት ፡ ቢኾን ፡ ያመኑት ፡ አሸሽተው ፡ ቤርያ ፡ ሰደውታል ፤ ቤርያ ፡ ገብቶ ፡ ቢያስተምር ፡ የቤርያ ፡ ሰዎች ፡ ትምህርቱን ፡ ተቀብለውታል ፡ ወፈድፋደ ፡ ይኄይሱ ፡ እለ ፡ በቤርያ ፡ እምእለ ፡ በተሰሎንቄ ፡ እንዲል ፡፡ ከዚያስ ፡ ማን ፡ አሰናብቶታል ፡ ብለው ፡ ሐደው ፡ የሚጣሉት ፡ ቢኾን ፡ የቤርያ ፡ ሰዎች ፡ አሸሽተው ፡ አቴና ፡ ሰደውታል ፡ በአቴና ፡ ኹኖ ፡ ጢሞቴዎስን ፡ ጠይቀሃቸው ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ሰዶታል ፡፡ ቢሔድ ፡ ያላመኑት ፡ ካመኑት ፡ ወገን ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ፈጅተውባቸው ፤ የቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ ኃዘን ፡ አዝነው ፤ ፍቅር ፡ መስሏቸው ፡ አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ ሚስት ፡ የሚደርሱ ፡ ሆነው ፡ አግኝቷቸዋል ፡ ሔዶ ፡ ይህን ፡ ነግሮታል ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ለዚህ ፡ ይጽፋል ፤ ወያአምር ፡ ኵሉ ፡ ለለአሐዱ ፡ አሐዱ ፡ ንዋዮ ፡ ወያጥርዮ ፡ በቅድሳት ፡ ወበክብር ፡ ወኢትትመንሰዉ ፡ በፍትወት ፡ ከመ ፡ አረሚ ፡ እለ ፡ ኢየአምርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይላል ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፬ ፡ ወንፈቅድ ፡ ታእምሩ ፡ አኃዊነ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ኖሙ ፡ ከመ ፡ ኢይደሉ ፡ ትተክዙ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ሰብአ ፡ እለ ፡ ቅቡጻን ፡ ተስፋሆሙ ፡ ይላል ፡ ም ፡ ፬ ፡ ፲፫ ፡ ናስተበቍዓክሙ ፡ አኃዊነ ፡ ዑቅዎሙ ፡ ለአለ ፡ ይጻምዉ ፡ በውስቴትክሙ ፡ ወለእለ ፡ ይቀውሙ ፡ ለክሙ ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ወይሜህሩክሙ ፡ ይላል ፡ (ም ፡ ፭ ፡ ፲፪ ፡)

ናስተበቍዓክሙ ፡ እኃዊነ ፡ ገሥጽዎሙ ፡ ለዘሉፋን ፡ ናዝዝዎሙ ፡ ለኅዙናን ፡ ጹርዎሙ ፡ ለድኩማን ፡ ይላል ፡ (፭፡ ፲፬፡) አምሀልክሙ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታንብብዋ ፡ ለዛቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ አኃዊነ ፡ ይላል ፡ (ም ፡ ፭ ፡ ፳፯ ፡፡

የተጻፈበት ፡ አገር ፡ አቴና ፡ ከታብ ፡ ወሳጅ ፡ ጢሞቴዎስና ፡ ስልዋኖስ ፡ ናቸው ፡፡

## ምዕራፍ ፡ ፩ ፡፡

፩ ፡ እምጳውሎስ ፡ ወስልዋኖስ ፡ ወጢሞቴዎስ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱ ፡ ፲፯ ፡ ፩ ፡ ፬ ፡ ፪ ፡ ተስ ፡ ፩ ፡ (፩ ፡፡)

ከኔ ፡ ከጳውሎስና ፡ ከስልዋኖስ ፡ ከጢሞቴዎስም ፡ የተላከች ፡ ከታብ ፤ ስልዋኖስ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ በጽሕፈትም ፡ በድርሰትም ፡ አግዘውት ፡ አይደለም ፡ ስለትሕትና ፡ ያነሣቸዋል ፡፡

ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘተሰሎንቄ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡፡

በእግዚአብሔር ፡ አብና ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ አምነው ፡ በተሰሎንቄ ፡ ላሉ ፡ እምመናን ፡ ትድረስ ፡፡

ሰላም ፡ ለክሙ ፡፡
ቸር ፡ አላችሁን ፡፡

ወጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡፡
የእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ጸጋው ፡ ይደርባችሁ ፡ ይደረግላችሁ ፡፡

፪ ፡ ነአኵቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘልፈ ፡ በእንቲአክሙ ፡፡
ስለናንት ፡ እግዚእብሔርን ፡ ኹልጊዜ ፡ እናመሰግነዋለን ፡፡

ወንዜክረክሙ ፡ ወትረ ፡ በጸሎትነ ፡፡
ኹልጊዜ ፡ በምንጸልየው ፡ ጸሎት ፡ ኹልጊዜ ፡ እናስባችኋለን ፡ ሐተታ ፡ እንዳለፈው ፡፡

፫ ፡ ወንዜክር ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ግብረ ፡ ሃይማኖትክሙ ፡ ወጻንዐ ፡ ፍቅርክሙ ፡ ወትዕግሥተ ፡ ተስፋክሙ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፳፱ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፲፫ ፡፡)

በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚኾን ፡ የአስኝታችሁን ፡ ትዕግሥት ፡ የፍቅራችሁን ፡ ብዛት ፡ የሃይማኖታችሁን ፡ ጽናት ፡ አስበን ፡ ነአኵቶ ፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ምክንያተ ፡ ጽሒፎቱ ፡ ለጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ መልእክተ ፡ ቀዳሚተ ፡ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ ተሰሎንቄ ፡ በእንተ ፡ መከራ ፡ ወምንዳቤ ፡ ብዙኅ ፡ ዘበጽሐ ፡ ላዕለ ፡ ምእመናን ፡ እምነ ፡ አዝማዲሆሙ ፡ እለ ፡ ኢአምኑ ።

ተሰሎንቄሰ ፡ እሐቲ ፡ መክፈልት ፡ ይእቲ ፡ እመቄዶንያ ።

ወይነብሩ ፡ ውስቴታ ፡ ምስለ ፡ አሕዛብ ፡ ኅቡረ ።

ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ጳውሎስ ፡ ኀቤሆሙ ፡ አመ ፡ ቀዳሚ ፡ ስብከቱ ፡ ኢአምኑ ፡ እለ ፡ ይበዝኁ ፡ ዘእንበለ ፡ ኅዳጣን ፡ ወባሕቱ ፡ አጽንዑ ፡ ላዕሌሁ ፡ ሕማመ ፡ ወምንዳቤ ፡ ብዙኀ ።

ወከማሁ ፡ አጽንዑ ፡ ምንዳቤ ፡ ወመከራ ፡ ላዕለ ፡ ምእመናን ።

ወእገበርዎሙ ፡ ከመ ፡ ይስግዱ ፡ ለአማልክት ፡ ወይሡዑ ፡ ሎሙ ።

ወአጽሐብዎሙ ፡ ብዙኀ ።

ወይበረብሩ ፡ ንዋዮሙ ፡ ወይሞቅሕዎሙ ፡ ወይቀትልዎሙ ።

ወበእንተዝ ፡ በገዐ ፡ ብካይ ፡ ወስቆቃው ፡ ላዕሌሆሙ ።

ወቀብጸ ፡ ለለ፩ ፡ ተስፋሁ ፡ ወፈቀዱ ፡ ይግብኡ ፡ ድኅሬሆሙ ።

ወበእንተዝ ፡ ጸሐፈ ፡ ሎሙ ፡ ዝንቱ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘንተ ፡ መልእክተ ።

እንዘ ፡ ይብል ፡ ወእፈቅድ ፡ ታእምሩ ፡ አኃዊነ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ኖሙ ፡ ከመ ፡ ኢይደሉ ፡ ትትከዙ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ ቅቡጻን ፡ ተስፋሆሙ ።

ወእምከመሰ ፡ ነአምን ፡ ከመ ፡ ሞተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወተንሥአ ፡ ከማሁ ፡ ያነሥኦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለምውታን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ወያመጽኦሙ ፡ ምስሌሁ ።
ወዘይትልዎ ፡ ለዝንቱ ።

ወበዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ቃሉ ፡ ያጽንዖሙ ፡ ከመ ፡ ኢያንቀልቅሉ ፡ ወሚጠ ፡ ልቦሙ ፡ ኀበ ፡ ሃይማኖት ።

ወዓዲ ፡ አዘዞሙ ፡ ለእለ ፡ ያበዝኁ ፡ ዝሙተ ፡ ወየኀድጉ ፡ ብእሲቶሙ ፡ ወየሐውሩ ፡ ብእሲተ ፡ ብእሲ ፡ ከመ ፡ ይትዐቀቡ ፡ ወይርኀቁ ፡ እምዝሙት ።

ወያእምር ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ ፡ ንዋዮ ፡ ወያጥርዮ ፡ በቅድሳት ፡ ወኢይትመንሰው ፡ በፍትወት ፡ ከመ ፡ አረሚ ።

ወጸሐፈ ፡ ዘንተ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በአቴና ፡ ወፈነዎ ፡ በእደ ፡ ቲኪቆስ ።

ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ለተሰሎንቄ ፡ ሰዎች ፡ የመጀመሪያይቱን ፡ ክታብ ፡ የጻፈበት ፡ ምክንያት ፡ በምእመናን ፡ ላይ ፡ ካላመኑ ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ብዙ ፡ ፈተና ፡ ችግር ፡ ስለደረሰባቸው ፡ ነው ።

ይች ፡ ተሰሎንቄም ፡ ከመቄዶንያ ፡ አንዲት ፡ ክፍል ፡ ናት ።

በውስጧ ፡ ምእመናን ፡ ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ይኖሩባት ፡ ነበረ ።

ጳውሎስ ፡ በመጀመሪያ ፡ ሰብከቱ ፡ ወደነሱ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ከጥቂቶች ፡ በቀር ፡ ብዙዎቹ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መከራ ፡ አጸኑበት ፡ እንጂ ፡ አላመኑም ፡ ነበረ ።

እንዲሁም ፡ በምእመናን ፡ ላይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መከራ ፡ አጸኑባቸው ።

ለጣዖት ፡ እንዲሰግዱ ፡ መሥዋዕት ፡ እንዲሠውላቸው ፡ ግድ ፡ አሏቸው ።

ብዙም ፡ አስጨነቋቸው ።
ገንዘባቸውን ፡ ይዘርፉዋቸው ፡ ያስሩዋቸው ፡ ይገሏቸው ፡ ነበረ ።

ስለዚህ ፡ ልቅሶና ፡ ኀዘን ፡ በዝቶባቸው ፡ ነበረ ።

አንዱም ፡ አንዱ ፡ ተስፋ ፡ ቆርጠው ፡ ከወንጌል ፡ ወደጣዖት ፡ ሊመለሱ ፡ ወደው ፡ ነበረ ።

ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ሐዋርያ ፡ ይህን ፡ ክታብ ፡ ጻፈላቸው ።

ወንድሞቻችን ፡ ስለሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ተስፋ ፡ ትንሣኤ ፡ እንደሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ አድርጋችሁ ፡ ልታዝኑ ፡ እንዳይገባ ፡ ልታውቁ ፡ እወዳለሁ ፡ እያለ ፡ ጻፈላቸው ።

ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ ካመን ፡ እንደዚሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምውታንን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በዠርነት ፡ ያስነሣቸዋል ።

ከሱም ፡ ጋራ ፡ ያመጣቸዋል ።

ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ቃል ፡ ጻፈላቸው ።

በዚህ ፡ ኹሉ ፡ ቃሉ ፡ እንዳይነዋወጡ ፡ እያጸና ፡ ልቡናቸውን ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ወንጌል ፡ መለሰ ።

ዳግመኛም ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ እየተው ፡ ከጕልማሳ ፡ ሚስት ፡ እየኼዱ ፡ ዝሙትን ፡ የሚያበዙትን ፡ ሰዎች ፡ ከዝሙት ፡ እንዲርቁ ፡ እንዲጠበቁ ፡ አዘዛቸው ።

አንዱም ፡ አንዱ ፡ ኹሉ ፡ ዐውቆ ፡ አካሉን ፡ በንጽሕና ፡ ይያዝ ፡ እንደ ፡ አረሚ ፡ በፍትወት ፡ ድል ፡ አይነሣ ፡ እያለ ፡ አዘዛቸው ።

በአቴና ፡ ሳለ ፡ ይህን ፡ ጽፎ ፡ በቲኪቆስ ፡ እጅ ፡ ላከው ።

www.ethiopianorthodox.org

፬ ፡ ወነአምር ፡ አኃዊነ ፡ ፍቁራን ፡ ዘከመ ፡ ኃረየክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ቈላ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።)
(ፍቁራን ፡ ) እግዚአብሔርን ፡ የምትወዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚወዳችሁ ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ የምትዋ
ደዱ ፡ ወንድሞቻችንን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደመረጣችሁ ፡ እናውቃለን ።

፭ ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ትምህርትነ ፡ ኀቤክሙ ፡ በነገር ፡ ባሕቲቱ ።
እናንተን ፡ ማስተማራችን ፡ በነገር ፡ ማፈቻል ፡ ብቻ ፡ አይደለምና ። ዓዲ ፡ በኃይልኒ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፭)
ድውይ ፡ በመፈወስ ፡ ምውት ፡ በማንሣት ፡ ጋኔን ፡ በማውጣት ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወበመንፈስ ፡ ቅዱስ ።
መንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ አሳድሮ ፡ ቋንቋ ፡ በማናገር ፡ ምሥጢር ፡ በመግለጽ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወበብዙኅ ፡ ምእመን ።
በታመነ ፡ መከሰስም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ (ዘትታ ፡ ) ሐዋርያት ፡ ይህ ፡ ይደረግልን ፡ ብለው ፡ አቅቷቸው ፡
የሚቀር ፡ የለምና ።
ወእንትሙኂ ፡ ተአምሩ ፡ ዘከመ ፡ ኮነ ፡ በኀቤክሙ ፡ በእንቲአክሙ ።
እኛም ፡ ስለእናንት ፡ ከናንት ፡ ዘንድ ፡ የኾነውን ፡ ታውቃላችሁ ፡ (እለ) ፡ መከራ ፡ እንደተቀበልነ ።

፮ ፡ ወናሁ ፡ ኪያነ ፡ ተመሰልክሙ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲፮ ።)
እነሆ ፡ አሁን ፡ እኛን ፡ መስላችኋል ።
ወተወከፍክሙ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በብዙኅ ፡ ሕማም ፡ ምስለ ፡ ፍሥሐ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ልጆች ፡ ኾናችሁ ፡ ከደስታ ፡ ጋራ ፡ በብዙ ፡ መከራ ። አንድም ፡ ከመከራ ፡ ጋራ ፡ በብዙ ፡
ደስታ ፡ ወንጌልን ፡ ተቀብላችኋልና ። አንድም ፡ ከልጅነት ፡ ጋራ ፡ በመከራው ፡ ደስ ፡ እያላችሁ ፡ ወን
ጌልን ፡ ተቀብላችኋልና ። ወፅኡ ፡ እምዐውደ ፡ አንዘ ፡ ይትፌሥሑ ፡ እስመ ፡ ከፈሎሙ ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ያኀሥርዎሙ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡ እንዲል ፡ ግብ ፡ (ሐዋ ፡ ፭ ፡ ፵፩ ። )
በዐደባባይ ፡ ገፈው ፡ ገርፈው ፡ ሲያወጧቸው ፡ እንደተሾሙ ፡ እንደተሸለሙ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋልና ።

፯ ፡ ወኮንክምዎሙ ፡ አርአያ ፡ ለእለ ፡ አምኑ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ በመቄዶንያ ፡ ወአካይያ ፡ (ም ፡ ፬ ፡ ፲ ። )
በአካይያ ፡ ቆሮንቶስና ፡ በመቄዶንያ ፡ ፊልጵስዩስ ፡ ላሉ ፡ ምእመናን ፡ አብነት ፡ ኾናችኋቸዋል ።

፰ ፡ እስመ ፡ እምኀቤክሙ ፡ ተምህሩ ፡ ቃለ ፡ እግዚእነ ፡ ወሰምዑ ።
ወንጌልን ፡ ከናንት ፡ ተምረው ፡ እምነዋልና ።
ወአኮ ፡ በመቄዶንያ ፡ ወአካይያ ፡ ባሕቲቱ ።
አብነትነታችሁም ፡ በአካይያ ፡ ቆሮንቶስና ፡ በመቄዶንያ ፡ ፊልጵስዩስ ፡ ላሉ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።
ዓዲ ፡ በኵሉ ፡ በሐውርት ፡ ተሰምዐት ፡ ሃይማኖትክሙ ፡ በእግዚአብሔር ፡ (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፰ ።
በእግዚአብሔር ፡ ማመናችሁ ፡ በአራቱ ፡ ማዕዝን ፡ ተሰምታልች ፡ እንጂ ።
ወኢንፈቅድ ፡ ንሕነ ፡ ምንተኒ ፡ ንንግር ፡ በእንቲአክሙ ።
እኛ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የናንተን ፡ ነገር ፡ ልንናገር ፡ አንሻም ።

፱ ፡ ለሊሆሙ ፡ የእምሩ ፡ ዘከመ ፡ በእነ ፡ ኀቤክሙ ።
ወደናንት ፡ በመምህርነት ፡ እንደመጣን ፡ ራሳቸው ፡ ያውቃሉና ።
ወዘከመ ፡ ተመየጥክሙ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምአምልኮ ፡ ጣዖት ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፪ ።)
በኛ ፡ ትምህርት ፡ ከአምልኮ ፡ ጣኦት ፡ ወደአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደተመለሳችሁ ፡ ያውቃሉና ።
ከመ ፡ ትትቀነዩ ፡ ለእምላክ ፡ ሕያው ።
ለምውቱ ፡ ትታችሁ ፡ ለሕያዉ ።
ወጻድቅ ።
ለሐሰተኛው ፡ ትታችሁ ፡ ለውነተኛው ፡ አምላክ ፡ ትገዙ ዘንድ ።

፲ ፡ እንዘ ፡ ትሴፈውዎ ፡ ለወልዱ ፡ እምሰማያት ፡ ዘተንሥአ ፡ እሙታን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፩
፲፩ ፡ ፊል ፡ ፫ ፡ ፳ ፡ ቲቶ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ።)
ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ የተነሣ ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ከወደሰማይ ፡ ይመጣል ፡ ብላ
ችሁ ፡ ተስፋ ፡ አድርጋችሁ ።
ወውእቱ ፡ ያድኀነነ ፡ እመንሡት ፡ ዘይመጽእ ።
ከሚመጣው ፡ መከራ ፡ ያድነናል ፡ ብላችሁ ፡ አንድም ፡ ዘተንሥአ ፡ ወያድኀነነ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

፩ ፡ ስሊክሙ ፡ ተእምሩ ፡ አኃዊነ ፡ ዘከመ ፡ ገብርነ ፡ ለክሙ ፡
ወንድሞቻችን ፡ እኛ ፡ ለናንት ፡ ያደረግነውን ፡ ነገር ፡ ራሳችሁ ፡ ታውቃላችሁ ።
ወኢኮነ ፡ በከንቱ ፡ በዊአትነ ፡ ኀቤክሙ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፭ ፡ ፲ ።)
እናንተን ፡ ማስተማራችን ፡ መከራ ፡ ባለመቀበል ፡ አይደለምና ።

፪ ፡ ዳዕሙ ፡ ሐመምነ ።
መከራ ፡ እየተቀበልን ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወተጽዕልነ ።
እየተዋረድን ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ዘከመ ፡ ተእምሩ ፡ በፊልጵስዩስ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፯ ፡ ፳፱ና ፡ ፲፯ ፡ ፭ ።)
በፊልጵስዩስ ፡ የተቀበልነውን ፡ እንደምታውቁ ።
ወእሜሃ ፡ ነገርናክሙ ፡ በብዙኅ ፡ ጻማ ፤ ትምህርተ ፡ ክርስቶስ ።
ያንጊዜ ፡ በብዙ ፡ ጻር ፡ የክርስቶስ ፡ ትምህርት ፡ ወንጌልን ፡ ነግረናችሁ ።
እንደነገርናችሁ ፡ ተእምሩ ።
በሞገሱ ፡ ለአምላክነ ።
በፈጣሪያችን ፡ አጋዥነት ።

፫ ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ትምህርትነ ፡ ዘስሒት ።
አሪትን ፡ የምናስተምር ፡ አይደለንምና ፡ (ሐተታ ፡ ) ስሒት ፡ አላት ፡ አሪትን ፡ ከስሕተት ፡ በኋላ ፡ስለ
ተሠራች ፡ ሕገ ፡ ተሰፋ ፡ አይደለችምና ፤ ቢጽ ፡ ሓሳዊ ፡ እየገባ ፡ ያስትባታልና ።
ወኢዘርኩስ ።
ኃጢአት ፡ የምትኾን ፡ አሪትን ፡ የምናስተምር ፡ አይደለምና ።
ወኢኮነ ፡ ዘጽልሑት ።
ክዳት ፡ ሽንገላ ፡ የምትኾን ፡ አሪትን ።

፬ ፡ ዳዕሙ ፡ በዘአመከረነ ፡ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፡ በመረመረን ፡ ገንዘብ ።
ወተአመነነ ፡ በትምህርተ ፡ ወንጌሉ ፡ (፩ ፡ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፩ ።)
ወንጌልን ፡ ለማስተማር ፡ ትበቃላችሁ ፡ ባለን ፡ ገንዘብ ።
ከማሁ ፡ ንነግር ።
ወንጌልን ፡ እናስተምራለን ፡ እንጂ ፡ (ከማሁ ) ፡ እሜሃ ፡ ነገርናክሙ ፡ በብዙኅ ፡ ጻማ ፤ ትምህርተ ፡ክር
ስቶስ ፡ ብየ ፡ እንደተናገርኩ ።
ወአኮ ፡ ከመ ፡ ዘለሰብእ ፡ ያደሉ ።
ማስተማራችንም ፡ ሰውን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ አይደለም ፡ ሰውን ፡ ደስ ፡ እንደሚያሰኝ ፡ አይደለም ።
ዘእንበለ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘአመከረነ ፡ ልበነ ። (ገላት ፡ ፩ ፲ ፡ ።)
የልቦናችንን ፡ መርምሮ ፡ የሚያውቅ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፭ ፡ ወእምእመ ፡ ኮነ ፡ ኢየዋህናክሙ ፡ በቃል ፡ በከመ ፡ ተእምሩ ።
ከኾነ ፡ ጀምሮ ፡ እንደ ፡ ምታውቁት ፡ መከራ ፡ የለባችሁም ፡ ብለንም ፡ በቃል ፡ አላስዘብናችሁም ።
ወኢተፀገልናክሙ ፡ በምክንያት ።
አስተምረናል ፡ ብለንም ፡ በምክንያት ፡ ክብታችሁን ፡ አልቀማናችሁም ።
ስምዕነ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዝንቱ ።
በዚህም ፡ ምስክራችን ፡ እሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

፮ ፡ ወኢንፈቅድ ፡ ያድሉ ፡ ለነ ፡ ሰብእ ። (ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፵፩ ፡ ፵፬ ።)
እኛስ ፡ ሰው ፡ ደስ ፡ ሊያሰኘን ፡ አንሻም ።
ኢእን ትሙ ።
እናንተም ፡ ኾኖ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወኢባዕድ ።

ሌላም ፡ ኾኖ ።

እንዘ ፡ ንከል ፡ አከብዶ ፡ ከመ ፡ ሐዋርያተ ፡ ክርስቶስ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡፳፡ ፴፫ ።)

ክርስቶስ ፡ የሾመን ፡ ሐዋርያት ፡ እንደመኾናችን ፡ እንድም ፡ ክርስቶስ ፡ እንደሾማቸው ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ አስተምሮ ፡ ዋጋ ፡ መብላት ፡ ሲገባን ፡ ኢተፀገልናከሙ ፡ ላለው ።

፯ ፡ ዳዕሙ ፡ ኮነ ፡ ከመ ፡ ሕፃናት ፡ ማእከሌከሙ ።

በናንት ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሕፃናት ፡ ኾነ ፡ (አለ) ፡ ሕፃን ፡ እበባውን ፡ አሳይቶ ፡ ግምጃውን ፡ ሎሚውን፡ አሳይቶ ፡ ወርቁን ፡ ቢወስዱበት ፡ እንዳያዝን ፡ እኛም ፡ አስተምረን ፡ ዋጋ ፡ ባለመቀበላችን ፡ ሳናዝን፡ አስተማርናችሁ ፡ እንጂ ፡ እንድም ፡ ሕፃናትን ፡ እንደሚያታልል ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፡ (አለ ።) ለሕፃን፡ አበባውን ፡ አሳይቶ ፡ ግምጃውን ፡ ሎሚውን ፡ አሳይቶ ፡ ወርቁን ፡ እንዲወስዱበት ፡ ዋጋ ፡ ያለመብላትን አሳይተን ፡ በትምህርት ፡ በሃይማኖት ፡ ገንዘብ ፡ አደረግናችሁ ፡ እንጂ ።

ወከመ ፡ ሐፃኒት ፡ እንተ ፡ ተሐዝል ፡ ደቂቃ ፡

ልጆቿን ፡ እንደምታሳድግ ፡ ሞግዚት ፡ ኾነ ፡ እንጂ ።

፰ ፡ ከማሁ ፡ ንሕነኒ ፡ ናፈቅረከሙ ።

ያች ፡ ልጆቿን ፡ እንድትወድ ፡ እኛም ፡ እንወዳችኋለን ።

ወንጽሕቅ ፡ ለከሙ ፡ ከመ ፡ ንመጡከሙ ።

ያች ፡ በወተት ፡ በፍትፍት ፡ እንድታሳድግ ፡ እኛም ፡ ወንጌልን ፡ እናስተምራችኋለን ።

ወአኮ ፡ ባሕቲቶ ፡ ወንጌለ ፡ እግዚአብሔር ።

ወንጌልን ፡ አስተምረናችሁ ፡ ብቻ ፡ የምንቀር ፡ አይደለም ።

ዓዲ ፡ ነፍሰነኒ ።

ሰውነታችንንም ፡ ለመከራው ፡ አሳልፈን ፡ እንሰጣለን ፡ እንጂ ።

እስመ ፡ ፍቁራነ ፡ ኮንከሙነ ።

በሃይማኖት ፡ መስላችሁናልና ።

፱ ፡ ወተዘከሩ ፡ እኃዊነ ፡ ጻማነ ፡ ወሥራሕነ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ኮነ ፡ ንትጌበር ። (፩፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፲፪ ።)

በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ ይዘን ፡ የደከምነውን ፡ ድካም ፡ አስቡት ፤ (ሌት ፡ በስፌት፡ ቀን ፡ በትምህርት ። )

ከመ ፡ ኢናከብድ ፡ ላዕለ ፡ አሐዱሂ ፡ እምውስቴትከሙ ።

ከናንት ፡ እንዱንስ ፡ እንኳ ፡ እንዳናስቸግር ፡ ከናንት ፡ ባንዱስ ፡ እንኳ ፡ ሥርዓት ፡ እንዳናጸና ።

፲ ፡ ወለሊከሙ ፡ ሰማዕትነ ።

እናንት ፡ ቅሉ ፡ ምስክሮቻችን ፡ ናችሁ ።

ወእግዚአብሔር ። እግዚአብሔርም ፡ ምስክራችን ፡ ነው ።

ዘከመ ፡ ሰበክነ ፡ ለከሙ ፡ ትምህርተ ፡ ወንጌሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በጽድቅ ፡ ወበርትዕ ፡ ወበንጽሕ ፡ በኀበ ኵሉሙ ፡ እለ ፡ የአምኑ ። (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፪ ።)

የእግዚአብሔር ፡ ትምህርት ፡ ወንጌልን ፡ በጽድቅ ፡ በርትዕ ፡ በንጽሕ ፡ እንዳስተማርናችሁ ፡ (አለ ፡) በጸጋ ፡ ዘነሣእከሙ ፡ በጸጋ ፡ ሀቡ ፡ በከንቱ ፡ ዘነሣእከሙ ፡ በከንቱ ፡ ሀቡ ፡ ባለው ፡ እንዳስተማርናችሁ ፡ በሚያምኑ ፡ በምእመናን ፡ ዘንድ ፡ ምስክሮቻችን ፡ ናችሁ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ምስክራችን ፡ ነው ።

፲፩ ፡ ዘከመ ፡ ተእምሩ ፡ ለለአሐዱ ፡ አሐዱ ፡ እምውስቴትከሙ ።

ከናንት ፡ እንዱም ፡ እንዱም ፡ እንደምታውቁ ፡ ምስክሮቻችን ፡ ናችሁ ።

ከመ ፡ አብ ፡ ለወልዱ ፡ ናስተበቍዓከሙ ።

አባት ፡ ልጁን ፤ ልጄ ፤ እንዲህ ፡ ብታደርግ ፡ ይሻል ፡ ይመስለኛል ፡ ብሎ ፡ እንዲያለዝብ ፡ እናለዝባ ችኋለን ።

፲፪ ፡ ወንናዝዘከሙ ።

አባት ፡ ልጁን ፡ እንዲያጽናናው ፡ እናጽናናችኋለን ።

ወናሰምዕ ፡ ለከሙ ።

እናዳኝባችኋለን ።

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ፡ ትሑሩ ፡ ወትሩጹ ፡ በዘይደልወክሙ ፡ ለኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘጸውዐክሙ ፡ ውስተ ፡ መንግሥተ ፡ ስብ
ሐቲሁ ፡ (ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፩ ፡ ፊል ፡ ፩ ፡ ፳፯ ።)

ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመሔድ ፡ በሚገባ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ እንድም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚገባ ትሔዱ ፡ ዘንድ ፡ በጌትነት ፡ ወደሠራት ፡ ወደወንጌል ፡ የጠራችሁ ።እንድም ፡ በጌትነት ፡ ወደሚያወርሳት ወደመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወደጠራችሁ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመሔድ ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

፲፫ ፡ በእንተዝ ፡ ንሕነኒ ፡ ዘልፈ ፡ ነአኵቶ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ስለዚህም ፡ እኛ ፡ ኹልጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናመሰግነዋለን ።

እስመ ፡ ተወከፍክሙ ፡ ቃለ ፡ ትእዛዙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወእኮ ፡ ቃለ ፡ ዜና ፡ ሰብእ ።

ዜና ፡ ሰብእ ፡ አሪትን ፡ ያይደለ ፡ እንበ ፡ እብለክሙ ፡ ብሎ ፡ የሠራት ፡ ወንጌልን ፡ ተቀብላችኋልና ። ዜና ፡ ሰብእ ፡ አላት ፡ኦሪትን ፡ በሙሴ ፡ በኢያሱ ፡ አድሮ ፡ ሠርቷታልና ።

እላ ፡ እማን ፡ ከማሁ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ።

(ከማሁ ፡) ተወከፍክሙ ፡ ቃለ ፡ ትእዛዙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዳልሁ ፡ ወንጌልን ፡ ተቀብላችኋል ፡ እንጂ ።

ወይረድአክሙኒ ፡ በግብር ፡ ለእለ ፡ ትአመንክሙ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፳ ፡ገላት ፡ ፩ ፡ ፲፩ ።)

ሥራ ፡ በመሥራትም ፡ ጊዜ ፡ ያመናችሁበት ፡ እናንተን ፡ ያጸናችኋል ።

፲፬ ፡ ወእንትሙ ፡ አኃዊነ ፡ ተመሰልክሙ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እለ ፡ በይሁዳ ፡ ምእመናን በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

ወንድሞቻችን ፡ እናንተም ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እምነው ፡ በብሔረ ፡ ይሁዳ ፡ ያሉ ፡ ምእመናንን ፡ መስላችኋቸዋል ።

እስመ ፡ ሐመምክሙ ፡ እንትሙኒ ፡ እምሕዝብክሙ ፡ በከመ ፡ ሐሙ ፡ እሙንቱኒ ፡ እምአይሁድ ፡ እለ ፡ቀተልዎ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ግብ፡ ሐዋ፡ ፪፡ ፳፱፡ ፲፫፡ ፴፫ ።)

እነሱ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ሰቅለው ፡ ከገደሉት ፡ ከአይሁድ ፡ መከራ ፡ እንደተቀበሉ ፡ እናንተም ፡ ከወገኖቻችሁ ፡ መከራ ፡ ተቀብላችኋልና ።

፲፭ ፡ ወለነቢያትኒ ፡ እለ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ሰደድዎሙ ።

ከነሱ ፡ ወገን ፡ የሚኾኑ ፡ ነቢያትን ፡ ሀገር ፡ እስዋለው ፡ ይሰዷቸው ፡ ከነበረ ፡ ከወገኖቻቸው ፡ ከአይ ሁድ ፡ መከራ ፡ እንደተቀበሉ ።

ወኪያነኒ ።

እኛንም ። ከዋልንበት ፡ እናሳድር ፡ ከአደርንበት ፡ እናውል ፡ ከሚሉ ፡ ከወገኖቻቸው ፡ ከአይሁድ ፡ መከራ ፡ እንደተቀበሉ ፡ እናንተም ፡ ከወገኖቻችሁ ፡ መከራ ፡ ተቀብላችኋልና ። እንድም ፡ እኛን ፡ ከዋል ንበት ፡ እናሳድር ፡ ከአደርንበት ፡ እናውል ፡ ከሚሉ ፡ ከወገኖቻችሁ ፡ መከራ ፡ ተቀብላችኋልና ።
እንድም ፡ተቀብላችኋልና ፡ ተመሰልክሙ ፡ ኪያነ ፡ እኛንም ፡ መስላችኋል ።

ወኢያሠምርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ከማያሰኙ ፡ ከአይሁድ ፡ መከራ ፡ እንደተቀበሉ ። እንድም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ከማያሰኙ ፡ ከወገኖቻችሁ ፡ መከራ ፡ ተቀብላችኋል ።

ወይትቃረኑ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ።

ከሰው ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ከሚጣሉ ፡ ከሚከራከሩ ፡ ከአይሁድ ፡ መከራ ፡ እንደተቀበሉ ። እንድም ፡ ከሰው ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ከሚጣሉ ፡ ከሚከራከሩ ፡ ከወገኖቻችሁ ፡ መከራ ፡ ተቀብላችኋልና ።

፲፮ ፡ ወይከልኡነ ፡ ኢንንግር ፡ ለአሕዛብ ፡ በዘየሐይዉ ፡ (ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፴፪ ፡ ፴፫ ።)

በሚያምኑ ፡ በሚድኑ ፡ ገንዘብ ፡ ለአሕዛብ ፡ እንዳናስተምር ፡ ከሚከለከሉብን ፡ ከአይሁድ ፡ መከራ ፡ እንደተቀበሉ ። እንድም ፡ በሚያምኑ ፡ በሚድኑ ፡ ገንዘብ ፡ ለአሕዛብ ፡ እንዳናስተምር ፡ ከሚከለከሉብን፡ ከወገኖቻችሁ ፡ መከራ ፡ ተቀብላችኋልና ።

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ፡ ይትፌጸሞሙ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ለዝሉፉ ።

ኃጢአታቸው ፡ በፍዳ ፡ ይፈጸምባቸው ፡ ዘንድ ፡ እጸንሐ ፡ ለአሞሬዎን ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ይትፌጸም ፡ ኃጢአቱ ፡ እንዲል ።

ወናሁ ፡ በጽሐሙ ፡ መቅሠፍቶሙ ፡ ዘሰዓለም ።

እነሆ ፡ ፍዳቸውም ፡ የማያልፍ ፡ ጽኑ ፡ ሥቃይ ፡ ተፈርዶባቸዋል ።

፲፯ ፡ ወንሕነሰ ፡ አኃዊነ ፡ ከመ ፡ ዕጓለ፡ ማውታ፡ ኮነ ፡ እምኔከሙ ፡ በዝ ፡ መዋዕል ፡ ለገጽ ፡ ዳዕሙ፡ (ሮሜ፡፩፡፲፩)

እኛ ፡ ግን ፡ ወንድሞቻችን ፡ በዚህ ፡ ወራት ፡ ከናንት ፡ የተነሣ ፡ ከናንት ፡ ተለይተን ፡ እንደ ፡ ድኃ ፡ አደግ ፡ ኾነ ።

ወአኮሰ ፡ እምልብ ።

እንዲህም ፡ ማለታችን ፡ ፊታችሁን ፡ ከማየት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከልቡናችን ፡ ተለይታችሁ ፡ አይደለም።

ወፈድፋደ ፡ ጽሕቅነ ፡ ንርአይ ፡ ገጸከሙ ።

ይልቁንም ፡ ፊታችሁን ፡ ልናይ ፡ እንወዳለን ።

፲፰ ፡ ወብዙኀ ፡ ፈቀድኩ ፡ እምጻእ ፡ ኀቤክሙ ፡ ለልየ ፡ ጳውሎስ ።

ከወደድሀ ፡ ማን ፡ ከለከለህ ፡ ትለኝ ፡ እንደኾነ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ጳውሎስ ፡ ወደናንት ፡ ልምጣ ፡፡ ወደድሁ ።

ምዕረ ፡ ወካዕበ ።

ብዙኀ ፡ ያለውን ፡ ምዕረ ፡ ወካዕበ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ ልመጣ ፡ ወደድሁ ። ወአዕቀፈኒ ፡ ማንሻ ፡ ነው ።

ወአዕቀፈኒ ፡ ሰይጣን ።

አንድም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወደናንት ፡ ልመጣ ፡ ወደድሁ ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ ሰይጣን ፡ አስነካከለኝ ።

መኑ ፡ ቅስፋነ ። (ፊልጵ ፡ ፱ ፡ ፲፯ ፡ ፳ ፡ ፩ ፡ ፩ ።)

እኛ ፡ አንተን ፡ ብናይ ፡ እንጂ ፡ እኛን ፡ ማየት ፡ ላንተ ፡ ምን ፡ ይረባሃል ፡ ምን ፡ ይጠቅምሃል ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ።

አለኝታችን ፡ ማነው ።

፲፱ ፡ ወፍሥሓነ ።

ደስታችን ፡ ማነው ።

ወአክሊለ ፡ ምክሕነ ።

የመመኪያችን ፡ ክብር ፡ ማነው ።

እኮኑ ፡ አንትሙ ፡ በቅድመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በምጽአቱ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በፊቱ ፡ መመኪያችን ፡ እናንተ ፡ አይደላችሁምን ።

፳ ፡ እስመ ፡ አንትሙ ፡ ክብርነ ፡ ወፍሥሓነ ፡ (ክብርነ ፡ ወፍሥሓነ ፡ በምጽአቱ ።) ጌታችን ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ደስታችን ፡ ክብራችን ፡ ናችሁና ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ ፡ ወስኢነነ ፡ ተዐግሦ ፡ አብደርነ ፡ ንንበር ፡ እቴና ፡ አሐተኔ ፡ ባሕቲተነ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፯ ፡ ፲፬ ፡ ፲፭ ።)

ነገር ፡ ግን ፡ መከራውን ፡ መታገሥ ፡ ቢሣነን ፡ ለብቻችን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ኹነን ፡ በአቴና ፡ መኖርን፡ ወደድን ። ወፈነውናሁ ፡ ማንሻ ፡ ነው ።

፪ ፡ ወፈነውናሁ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ እኁነ ፡ ላእከ ፡ እግዚአብሔር ።

እናንተ ፡ ደስታችን ፡ ክብራችን ፡ ናችሁና ፡ ስለኾናችሁ ፡ ብቻችንን ፡ ለብቻችን ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ኾነን ፡ አቴና ፡ መኖርን ፡ ወደን ፡ ዝም ፡ ማለት ፡ ቢሳነን ። (ፈነውናሁ ።) የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ የሚኾን ፡ ወንድማችን ፡ ጢሞቴዎስን ፡ ሰደድነው ።

ወረድኤትነ ፡ በትምህርተ ፡ ክርስቶስ ።

የክርስቶስ ፡ ወንጌልን ፡ በማስተማር ፡ አጋዣችን ፡ የሚኾን ።

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ፡ ያጽንዕክሙ ።
　　በሃይማኖት ፡ ያጸናችሁ ፡ ዘንድ ።
ወያስተብቍዕክሙ ።
　　ይመክራችሁ ፡ ያስተምራችሁ ፡ ዘንድ ።
በእንተ ፡ ሃይማኖትክሙ ።
　　ስለሃይማኖታችሁ ፡ ያጸናችሁ ፡ ዘንድ ።

፫ ፡ ከመ ፡ ኢታንቀልቅሉ ።
　　እንዳትነዋወጡ ፡ በሃይማኖት ፡ ያጸናችሁ ፡ ዘንድ ።
ወኢይቅብጽ ፡ አሐዱሂ ፡ እምውስቴትክሙ ፡ በዛቲ ፡ ሕማምክሙ ፡ (ኤፌ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ። ፪ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።)
　　በዚች ፡ በመከራችሁ ፡ ከናንተ ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ የቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ ኃዘን ፡ እንዳያዝን ፡ ያስተብቍ
　ዕክሙ ።
ተአምሩ ፡ ለሊክሙ ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ዳዕሙ ፡ ይጸንሐነ ።
　　በሐድንበት ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ እንዲቆየን ፡ ታውቃላችሁ ።

፬ ፡ ወእመ ፡ ሀሎኩ ፡ ኀቤክሙ ፡ ዘንተ ፡ ከመ ፡ አቅደምኩ ፡ ወነገርኩክሙ ።
　　ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ በነበርሁ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሜ ፡ ይህን ፡ ነግሬያችሁ ፡ ነበር እንደነበረ ፡ ታውቃላችሁ
ከመ ፡ ሀለወነ ፡ ንሕምም ።
　　መከራ ፡ እንቀበል ፡ ዘንድ ፡ እንዳለን ።
ወይሣቅዩነ ።
　　ሥቃይ ፡ ያጸኑብን ፡ ዘንድ ፡ እንዳለን ፡ ነግሬያችሁ ፡ ነበር ።
ወበከመ ፡ አመርናክሙ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ።
　　እንደነገርናችሁ ፡ ያው ፡ የነገርናችሁ ፡ ኾነ ። አንድም ፡ በኛ ፡ እንደነገርናችሁ ፡ በኛ ፡ የነገርናችሁ ፡
　በናንተ ፡ ኾነ ።

፭ ፡ ወበእንተዝ ፡ እንሂ ፡ ስኢንየ ፡ ተዐግሦ ፡ ፈነውኩ ፡ ጢሞቴዎስሃ ።
　　ስለዚህ ፡ መከራውን ፡ መታገሥ ፡ ቢሳነኝ ። አንድም ፡ ዝም ፡ ማለት ፡ ቢሳነኝ ፡ ወደናንተ ፡ ጢሞቴ
　ዎስን ፡ ሰደድሁ ።
ከመ ፡ አእምር ፡ ሃይማኖተክሙ ።
　　የሃይማኖታችሁን ፡ ጽናት ፡ ፀውቅ ፡ ዘንድ ።
አመቦ ፡ ከመ ፡ አመከረክሙ ፡ ዘያሜክር ።
　　የሚፈታተን ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ ተፈታትኗችሁ ፡ እንደኾነ ፡ ብዬ ፤ የተፈታተናችሁ ፡ መፈታተን እንዳለ
　ብዬ ።

ወለከንቱ ፡ ይከውን ፡ ጻማነ ፡ ዘበእንቲአክሙ ። (ፊል ፡ ፪ ፡ ፲፮ ።)
　　እንዲህ ፡ የኾነ ፤ እንደኾነ ፡ ስለናንተ ፡ የደከምነው ፡ ድካም ፡ ዋጋ ፡ ላለመቀበል ፡ ይኾናል ፡ ብዬ ።
፮ ፡ ወይእዜሰ ፡ እምአመ ፡ በጽሐ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ኀቤነ ፡ እምኀቤክሙ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፰ ፡ ፭ ።)
　　ዛሬ ፡ ግን ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ ደርሶ ፡ ወደኛ ፡ ከመጣ ፡ ጀምሮ ፡ ከመጣ ፡ ወዲህ ።
ወዜነወነ ፡ ሃይማኖተክሙ ፡ ወተፋቅሮተክሙ ።
　　የሃይማኖታችሁን ፡ ጽናት ፡ የፍቅራችሁን ፡ ብዛት ፡ ከነገረን ፡ ጀምሮ ፤ ከነገረን ፡ ወዲህ ።
ወከመሂ ፡ ትዜከሩነ ፡ በሠናይ ፡ ዘልፈ ።
　　ኹልጊዜ ፡ በበጎ ፡ ነገር ፡ እንድታስቡን ፡ ከነገረን ፡ ጀምሮ ፤ ከነገረን ፡ ወዲህ ።
ወትፈትዉ ፡ ትርአዩነ ፡ በከመ ፡ ንፈቱ ፡ ንሕነሂ ፡ ርእዮተክሙ ።
　　እኛ ፡ እናንተን ፡ ልናያችሁ ፡ እንድንወድ ፡ እናንተም ፡ እኛን ፡ ልታዩን ፡ እንድትወዱ ፡ ከነገረን ፡
　ጀምሮ ፤ ከነገረን ፡ ወዲህ ።

፯ ፡ በእንተዝ ፡ ተፈሣሕነ ፡ አኃዊነ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ሕማምነ ፡ ወምንዳቤነ ፡ ዘበእንተ ፡ ሃይማኖትክሙ ፡
　　(ም ፡ ፪ ፡ ፪ ።)
　　ስለዚህ ፡ ስለ[illegible] ፡ [illegible]ችን ፡ የዘምትው ፡ መከራችን ፡ ደስ ፡ አለን ።

www.ethiopianorthodox.org

፰ ፡ እስመ ፡ ይእዜ ፡ ነሐዩ ፡ እምከመ ፡ አንትሙ ፡ ቆምክሙ ፡ በእግዚእነ ።
እናንተ ፡ በጌታችን ፡ በማመን ፡ ብትጸኑ ፡ ደስ ፡ ብሎናልና ። ወሐይወ ፡ ልቡ ፡ ለያዕቆብ ፡ እንዲል ፡ (ዘፍጥ ፡ ፵፭ ፡ ፳፯ ።)

፱ ፡ አየ ፡ አኰቴተ ፡ ማንሻ ፡ አየ ፡ አኰቴተ ንከል ፡ ዐሥዮቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሀየንተ ፡ ኵሉ ፡ ፍሥሐነ ፡ ዘተፈሣሕነ ፡ በእንቲአክሙ ፡ በጌታችን ፡ በማመን ፡ ብትጸኑ ፡ ደስ ፡ ብሎናልና ። ስለዚህ ፡ በናንተ ፡ ደስ ፡ ስላለን ፡ ደስታ ፤ ለእግእብሔር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ምስጋና ፡ ልናቀርብለት ፡ ይገባናል ።
ምንተኑ ፡ እዐሥዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ዘገብረ ፡ ሊተ ፡ ካለው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።
ዘእንበለ ፡ ከመ ፡ ንጼሊ ፡ ኀበ ፡ አምላክነ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ።
በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ወደፈጣሪያችን ፡ እንጸልያለን ፡ እንጂ ፡ ከመጸለይ ፡ በቀር ። ጽዋዐ ፡ ሕይወት ፡ እትሜጦ ፡ ወስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጼውዕ ፡ ካለው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

፲ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ንጼሊ ። ከመ ፡ ንርአይ ፡ ገጸክሙ ።
ይልቁንም ፡ ፊታችሁን ፡ እናይ ፡ ዘንድ ፡ እንጸልያለን ።
ወይትፈጸም ፡ ሕጸጸ ፡ ሃይማኖትክሙ ።
የሃይማኖታችሁ ፡ ሕጸጽ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ።

፲፩ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያርትዕ ፡ ፍናተነ ፡ ኀቤክሙ ።
የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የባሕርይ ፡ አባቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደናንተ ፡ መንገዳችንን ፡ ይቅናልን ፡ ያቀናልን ፡ ዘንድ ፡ ንጼሊ ።
፲፪ ፡ ወለክሙሂ ፡ ያብዝኀ ፡ ወያፈድፍድ ፡ ተፋቅሮተክሙ ፡ በበይናቲክሙ ።
እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ በፍቅር ፡ ፍጹማን ፡ ያድርጋችሁ ።
ወምስለ ፡ ኵሉ ፡ ለለ ፡ አሐዱ ።
በበይናቲክሙ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ከየአንዳንዱ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ።
ከመ ፡ ንሕነ ፡ ናፈቅረክሙ ፡ ለክሙ ።
እኛ ፡ እናንተን ፡ እንደምንወዳችሁ ።

፲፫ ፡ ወይጽናዕ ፡ ልብክሙ ፡ በንጽሕ ፡ ወበቅድሳት ። (፪ ፡ ተሰ ፡ ፪ ፡ ፲፯ ። ፊል ፡ ፩ ፡ ፲ ።)
ልቡናችሁ ፡ በንጽሕና ፡ በቅድስና ፡ ጸንቶ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ።
ለቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ እመ ፡ ምጽአተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መላእክትን ፡ አስከትሎ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ (ለቅድሜሁ ፡) ለባለሟሎች ፡ ለመኾን ፡ (በቅድሜሁ ፡) በፊቱ ፡ ለመቆም ።

---

ምዕራፍ ፡ ፬ ።

ክፍል ፡ ፫ ።

፩ ፡ ወይእዜኒ ፡ አኃዊነ ፡ ንነግረክሙ ።
አሁንም ፡ ወንድሞቻችን ፡ እንነግራችኋለን ።
ወናስተበቍዐክሙ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (፪ ፡ ተሰ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።)
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ማላጅ ፡ አድርገን ፡ እንማልዳችኋለን ።
ከመ ፡ ተአዘዝክሙ ፡ በኀቤነ ፡ በዘይደሉ ፡ ከመ ፡ ትሁሩ ፡ (ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፩ ።)
ከኛ ፡ እንደተማራችሁ ፡ በሚገባ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ።
ወታሥምርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።
እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ታሰኙት ፡ ዘንድ ።
ወበከመ ፡ ሖርክሙ ፡ ዓዲ ፡ ከመ ፡ ታብዝኁ ፡ ወታፈድፍዱ ፡ በዝንቱ ።
ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ ትሠሩት ፡ እንደነበረ ፡ እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ይህን ፡ አብዝታችሁ ፡ ትሠሩት ፡ ዘንድ ፡ እንማልዳችኋለን ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ ፡ ወተአምሩ ፡ ዘከመ ፡ አዘዝናክሙ ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡
ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ታዝዘን ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ክርስቶስ ፡ አዝዟችኋል ፡ ብለን ፡ አንደ ነገርናችሁ ፡ ታውቃላችሁ ።
፫ ፡ እስመ ፡ ዝውእቱ ፡ ትእዛዙ ፡ ለእግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔር ፡ ትእዛዙ ፡ ይህ ፡ ነውና ።
ወፈቃዱ ።
ፈቃዱም ፡ ይህ ፡ ነውና ።
ተቀድሶትክሙ ፡ ውእቱ ።
ንጽሕና ፡ መያዛችሁ ፡ ነውና ።
ወከመ ፡ ትትዓቀቡ ፡ ወትርኃቁ ፡ እምዝሙት ።
ከዝሙት ፡ ትከለከሉ ፡ ዘንድ ፡ ነውና
፬ ፡ ወያእምር ፡ ዙሉ ፡ ለለአሐዱ ፡ ንዋዮ ፡ ወያጥርዮ ፡ በቅድሳት ፡ ወክብር ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፫ ፡ ፲፰ ።)
እንዱም ፡ እንዱም ፡ አባለ ፡ ዘሩን ፡ ዐውቆ ፡ በንጽሕና ፡ ገንዘብ ፡ ያድርግ ፡ ዘበእንተ፡ ንዋይየ፡ ተቀደ ሰት ፡ ሊተ ፡ እንዲል ፡ (ሳሙ ፡ ቀዳ ፡ ፳፩ ፡ ፭ ።)
፭ ፡ ወኢትትመንሰዉ ፡ በፍትወት ፡ ከመ ፡ አረሚ ፡ እለ ፡ ኢያእምርዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ (ቈላ ፡ ፫ ፡ ፭ ።)
እግዚአብሔርን ፡ እንደማያውቁት ፡ እንደአረሚ ፡ በፈቲው ፡ ጾር ፡ ድል ፡ አትነሡ ።
ወኢትትሐበሉ ፡ ትግበሩ ፡ ዘንተ ።
ይህን ፡ ልትሠሩ ፡ አትውደዱ ፡ (ወይትሔበሉ) ፡ ይህን ፡ ሊሠሩ ፡ እንደሚወዱ ፡ እንደአረሚ ።
፮ ፡ ወኢትትአበዩ ።
አትታበዩ ፡ (ወይትኤበዩ) ፡ እንደሚታበዩ ።
ወኢትትእገሉ ፡ ቢጸከሙ ፡ በዙሉ ።
ወንድሞቻችሁን ፡ በሥራ ፡ ኹሉ ፡ አትቀሙ ፡ (ወይትኤገሉ ፡) ወንድሞቻቸውን ፡ እንደሚቀሙ ፡ አረሚ ፡ በፈቲው ፡ ጾር ፡ ድል ፡ አትነሡ ።
እስመ ፡ መስተበቅል ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ዙሉ ።
በዚህ ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈታሒ ፡ ነውና ።
በከመ ፡ አቅደምኩ ፡ ነጊሮተከሙ ።
አስቀድሜ ፡ በቆሮንቶስ ፡ ከመ ፡ ዓማፅያን ፡ ወዘማውያን ፡ ኢይወርስዋ ፡ ለመንግሥተ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ብዬ ፡ እንደነገርኋችሁ ። ያንዱንስ ፡ ለአንዱ ፡ እያመጣም ፡ ብሎ ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ እንደነገር ኋችሁ ።
ወአስማዕኩ ፡ ለክሙ ።
እንደአዳኘሁባችሁ ።
፯ ፡ እስመ ፡ ኢጸውዐነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለርኩስ ፡ ዘእንበለ ፡ ለቅድሳት ፡ (፪ ፡ ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፱ ።)
እግዚአብሔር ፡ ለንጽሕና ፡ እንጂ ፡ ለዝሙት ፡ አልጠራንምና ።
፰፡ ወይእዚኒ ፡ ዘክሕደሰ ፡ አኮ ፡ ለሰብእ ፡ ዘይክሕድ ።
እሁንም ፡ እኔን ፡ አሉ ፡ ያለ ፡ እኔን ፡ አሉ ፡ ያለ ፡ አይደለም ።
ዘእንበለ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘወሀበክሙ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፲፮ ።)
እግዚአብሔርን ፡ አሉ ፡ ያለ ፡ ነው ፡ እንጂ ። አንድም ፡ የኔን ፡ ሥርዓት ፡ ያፈረሰ ፡ የኔን ፡ ሥርዓት ፡ ያፈ ረሰ ፡ አደለም ።
ዘእንበለ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ልጅነትን ፡ የሰጠ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥርዓት ፡ ያፈረሰ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንድም ፡ ወይእዚኒ ፡ ዘክሀደ አኮ ፡ ለሰብእ ፡ ዘይክሀድ ።
ክርስቶስን ፡ የካደ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲን ፡ የካደ ፡ አይደለም፡ ልጅነትን ፡ የሰጠ ፡ እግዚአብሔርን፡ የካደ፡ ነው እንጂ ። ልጅነትን ፡ የሰጠ ፡ ብሎ ፡ ለአብ ፡ ይቀጥላል ።
፱ ፡ ወበእንተሰ ፡ አፍቅሮ ፡ ቢጽክሙ ፡ ኢትፈቅዱ ፡ ንጽሐፍ ፡ ለክሙ ፡(ማር ፡ ፲፪ ፡ ፴፩ ፤ ኤር ፡ ፴፩ ፡ ፴፫፡፴፬።
የፍቅረ ፡ ቢጽንስ ፡ ነገር ፡ እንጽፍላችሁ ፡ ዘንድ ፡ አትሹም ፡ አትሹ ።

www.ethiopianorthodox.org

ለሊክሙ ፡ ምሁራን ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ትትፋቀሩ ፡ በበይናቲክሙ ።
እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ፍቅርን ፡ ትይዙ ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተምራችሁ ፡ ዐውቃችኋልና ፡ ኢት
ፈቅዱ ።
፲ ፡ ወከማሁ ፡ ትገብሩ ፡ ዓዲ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ አኃዊነ ፡ እለ ፡ በኵሉ ፡ መቄዶንያ ፡ (፩ ፡ ፯ ።)
ዳግመኛም ፡ በመቄዶንያ ፡ካሉ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ እንደዚሁ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ምሁራን ፡
ናችሁና ፡ ኢትፈቅዱ ።
ወናስተበቍዐክሙ ፡ አኃዊነ ፡ ትብዝኁ ፡ ወትፈድፍዱ ። (ም ፡ ፬ ፡ ፩ ።)
ወንድሞቻችን ፡ ፍጹማን ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ኹኑ ፡ ብለን ፡ እንማልዳችኋለን ።
፲፩ ፡ ከመ ፡ ትኩኑ ፡ የዋሃነ ፡ የዋሃን ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ።
ወትትገበሩ ፡ ተግባረክሙ ፡ ወትትቀነዩ ፡ በእደዊክሙ ፡ (፪ ፡ ተሰ ፡ ፫ ፡ ፰ ፡ ፲፪ ፤ ም ፡ ፪ ፡ ፱ ።)
ተግባረ ፡ እድ ፡ ይዛችሁ ፡ ትመገቡ ፡ ዘንድ ፡ እንማልዳችኋለን ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ ይዞ ፡ መመገብን ፡ የዋ
ሃት ፡ እላት ።
ዘከመ ፡ አዘዝናክሙ ።
ለይትገበር ፡ ወይጸሙ ፡ በእዴሁ ፡ በሠናይ ፡ በዘይረድእ ፡ ለነዳይ ፡ ብለን ፡ እንደነገርናችሁ ። ያንዱንስ ፡
ለአንዱ ፡ እያመጣም ፡ ብሎ ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ እንደነገርናችሁ ።
፲፪ ፡ ከመ ፡ ትሑሩ ፡ በኂሩት ፡ በቅድመ ፡ እለ ፡ እፍአ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፲፫ ።)
ከምግባር ፡ ከሃይማኖት ፡ እፍአ ፡ ባሉ ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡ በበጎነት ፡ ትነሡ ፡ ዘንድ ፡ ።
ወኢትጽሐቁ ፡ ወኢኀበ ፡ መኑሂ ።
ከማንም ፡ ከማን ፡ ምግብ ፡ እትሹ ። እንዳትሹ ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ ይዛችሁ ፡ እንድትመገቡ ፡ እንማልዳ
ችኋለን ።

## ክፍል ፡ ፬ ።

፲፫ ፡ ወንፈቅድ ፡ ታእምሩ ፡ አኃዊነ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ኖሙ ፡ ከመ ፡ ኢይደሉ ፡ ትተክዙ ፡ በላዕሌሆሙ ፡ ከመ
ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ ቅቡጻን ፡ ተስፋሆሙ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፳ ፤ ኤፌ ፡ ፪ ፡ ፲፪ ።)
ወንድሞቻችን ፤ ስለሞቱ ፡ ሰዎች ፡ የቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ ኃዘን ፡ እንደሚያዝኑ ፡ እንደአሕዛብ ፡ የቁቢጸ ፡
ተስፋ ፡ ኃዘን ፡ ታዝኑ ፡ ዘንድ ፡ እንዳይገባ ፡ ልታውቁ ፡ እንወዳለን ።
፲፬ ፡ ወእምከመሰ ፡ ንትአመን ፡ ከመ ፡ ሞተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወተንሥአ ።
ክርስቶስ ፡ እንደሞተ ፡ እንደተነሣ ፡ ካመነ ።
ከማሁ ፡ ያነሥኦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለምውታን ፡ በኢየሱስ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፬ ፡ ፱ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፫ ፡ ፬ ።)
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በኩርነት ፡ እግዘአብሔር ፡ ሙታንን ፡ ያስነሣቸዋል ። እንዲያስነሣቸው ፡
እናውቃለንና ፤ ኢይደሉ ።
ወያመጽኦሙ ፡ ምስሌሁ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ አስከትሏቸው ፡ ይመጣል ።
፲፭ ፡ ወዘንተ ፡ ንነግረክሙ ፡ በቃለ ፡ እግዚአብሔር ።
ይህንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ታዝዘን ፤ እግዚአብሔር ፡ አዝዟችኋል ፡ ብለን ፡ እንነግራችኋለን ።
ንሕነ ፡ ሕያዋን ፡ እለ ፡ ንተርፍ ፡ እመ ፡ ምጽአተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢንበጽሖሙ ፡ ለምውታን ።
(፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፳፫ ፡ ፶፩ ።)
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ሕያዋን ፡ ኾነን ፡ የምንኖር ፡ እኛ ፡ ሙታንን ፡ እንቀድ
ማቸውም ።
፲፮ ፡ እስመ ፡ ይኤዝዝ ፡ እግዚእነ ፡ ምስለ ፡ ቃለ ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፳፫ ፡ ፶፪ ።)
ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘያነቅሖሙ ፡ ለምውታን ፡ ተብሎ ፡ በቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ቃል ፡ ከመመስገን
ጋራ ።
ወንፍሐተ ፡ ቀርን ፡ ዘእግዚአብሔር ።
ንቃሕ ፡ መዋቲ ፡ ዘትነውም ፡ ብሎ ፡ ፀዋጅ ፡ ከመንገር ፡ ጋራ ፤ ግብር ፡ እምግብር ፡ እንድንለወጥ ፡
ያዝዛልና ።

www.ethiopianorthodox.org

ዘይወርድ ፡ እምሰማይ ።

ምድራዊ ፡ ፀዋጅ ፡ እለና ፡ ከዚያ ፡ ሲለይ ፡ ዘይወርድ ፡ እምሰማይ ፡ አለ ።

ወይትነሥኡ ፡ ምውታን ፡ መቅድመ ፡ እለ ፡ ሞቱ ፡ በሃይማኖተ ፡ ክርስቶስ ።

በክርስቶስ ፡ እምነው ፡ የሞቱ ፡ ሰዎች ፡ አስቀድመው ፡ ይነሣሉ ።

፲፯ ፡ ወእምዝ ፡ ንሕነ ፡ ሕያዋን ፡ እለ ፡ ንትርፍ ፡ ንትመሠጥ ፡ በደመና ፡ ምስሌሆሙ ፡ ኅቡረ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሕያዋን ፡ ኾነን ፡ የምንኖር ፡ እኛ ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ኾነን ፡ በክብር ፡ እናርጋለን።

ከመ ፡ ንትቀበሎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ውስተ ፡ አየር ።

ጌታችነን ፡ በልዕልና ፡ እንዋሐደው ፡ ዘንድ ።

ወንሄሉ ፡ እንከ ፡ ዘልፈ ፡ ኀበ ፡ እግዚእነ ፤ (ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ፤ ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፳፯ ፤ ፲፯ ፡ ፳፬ ።)

ከሱ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕደን ፡ እንኖራለን ።

፲፰ ፡ ወይእዜኒ ፡ መሀሩ ፡ ቢጸክሙ ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ።

አሁንም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ለወንድሞቻችሁ ፡ አስተምሩ ።

---

## ምዕራፍ ፡ ፭ ።

፩ ፡ ወበእንተሰ ፡ ዕድሜሁ ፡ ወዕለቱ ፡ ወጊዜሁ ፡ እኀዊነ ፡ ኢትፈቅዱ ፡ ንጽሐፍ ፡ ለክሙ ፡ (ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፴፮)

የዘመኑን ፤ የዕለቱን ፡ ፤ የሰዓቱን ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ወንድሞቻችን ፡ እንጽፍላችሁ ፡ ዘንድ ፡ አትሹም ፡ አትሹ ፡ (ሐተታ ፡) ምነው ፡ ወርኁ ፡ ወርኀ ፡ መጋቢት ፡ ዘመኑ ፡ ዘመነ ፡ ዮሐንስ ፡ ዕለቱ ፡ ዕሰተ ፡ እሑድ ፡ ጊዜው ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ እንደኾነ ፡ ታውቆ ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፡ ብዙ ፡ ዘመነ ፡ ዮሐንስ ፡ ብዙ ፡ ወርኀ ፡ መጋቢት ፡ ብዙ ፡ ዕለተ ፡ እሑድ ፡ እለ ፡ ከዚያ ፡ ተለይቶ ፡ ስላልታወቀ ።

፪ ፡ ለሊክሙ ፡ ተአምሩ ፡ ጥዩቀ ፡ ከመ ፡ ዕለተ ፡ እግዚእነ ፡ ከመ ፡ ምጽአተ ፡ ሰራቂ ፡ ሌሊተ ። (ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፵፪ ፡ ፵፬ ፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲ ፡ ራእ ፡ ፫ ፡ ፫ና ፡ ፲፮ ፡ ፲፭ ።)

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚመጣበት ፡ ዕለቱ ፡ ምጽአት ፡ እንደሌባ ፡ አመጣጥ ፡ ድንገት ፡ ሌሊት ፡ እንደኾነ ፡ ታውቃላችሁና ።

ከማሁ ፡ ይከውን ፡ ምጽአቱ ።

ሌባ ፡ ባላወቁት ፡ ሰዓት ፡ ባልጠረጠሩት ፡ ዕለት ፡ እንዲመጣ ፡ የጌታም ፡ አመጣጡ ፡ ድንገት ፡ እንደ ኾነ ፡ ታውቃላችሁ ።

፫ ፡ አመ ፡ ይብሉ ፡ እለ ፡ ይከሀዱ ፡ ኪያሁ ፡ ከመ ፡ ውስቱ ፡ ዳኅን ፡ ወሰላም ፡ እሙንቱ ፡ ወሀየ ፡ ግብተ ፡ ይመ ጽእሙ ፡ ተሠርዎ ። (ኤር ፡ ፮ ፡ ፲፬ ፡ ፰ ፡ ፲፩ ።)

እሱን ፡ የካዱ ፡ ሰዎች ፡ በወዲሁ ፡ አለን ፡ አለን ፡ ሲሉ ፡ ድንገት ፡ መነቀል ፡ ይመጣባቸዋል ። መተከ ልን ፡ መደብ ፡ አድርጎላቸው ፡ መነቀል ፡ ይመጣባቸዋል ፡ አለ ።

ከመ ፡ ፀንሰት ፡ እንተ ፡ ይመጽእ ፡ ሕማም ።

ምጥ ፡ እንደተያዘች ፡ ሴት ።

ወኢይክሉ ፡ እምሥጠ ።

ያች ፡ መዳን ፡ እንዳይቻላት ፡ እነሱም ፡ መዳን ፡ አይቻላቸውም ።

፬ ፡ ወአንትሙሰ ፡ እኅዊነ ፡ ኢሀለዉክሙ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ከመ ፡ ይርከብክሙ ፡ ውእቱ ፡ ዕለት ፡ ከመ ፡ ሰራቂ ። (ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፰ ።)

እናንተ ፡ ግን ፡ ወንድሞቻችን ፡ ዕለተ ፡ ሞት ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፤ ፡ እንደሌባ ፡ አመጣጥ ፡ ድንገት ፡ ይደ ርስባችሁ ፡ ዘንድ ፡ ዐላዋቆች ፡ አይደላችሁም ።

፭ ፡ እስመ ፡ ኵልክሙ ፡ ውሉደ ፡ ብርሃን ፡ አንትሙ ፡ ወውሉደ ፡ መዓልት ። (ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፲፪ ፤ ኤፌ ፡ ፭፡፱።)

ኹላችሁም ፡ የዕውቀት ፤ የወንጌል ፡ ልጆች ፡ ናችሁና ።

ወኢኮንክሙ ፡ ውሉደ ፡ ሌሊት ፡ ወኢውሉደ ፡ ጽልመት ።

የድንቁርና ፡ የአሪት ፡ ልጆች ፡ አይደላችሁምና ፡ ኢሀለዉክሙ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ።

www.ethiopianorthodox.org

፮ ፡ ወኢንኑም ፡ እንከ ፡ ከመ ፡ እልኩ ።
 እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ ውሉደ ፡ ሌሊት ፡ ውሉደ ፡ ጽልመት ፡ እንደተባሉ ፡ እንደ ፡ ኀምስ ፡ አብዳት ፡ የን
 ዋመ ፡ ሐኬት ፡ እንቅልፍ ፡ አናንቀልፋ ።
አላ ፡ ንንቃህ ።
 ውሉደ ፡ ብርሃን ፡ ውሉደ ፡ መዓልት ፡ እንደተባሉ ፡ እንደ ፡ ኀምስ ፡ ጠባባት ፡ ከንዋመ ፡ ሐኬት ፡ እን
 ንቃ ፡ እንጂ ።
ወንትጋሀ ፡ ወንጠበብ ።
 እንትጋ ፡ እንራቀቅ ፡ እንጂ

፯ ፡ እስመ ፡ እለ ፡ ይነውሙ ፡ ሌሊተ ፡ ይነውሙ ።
 የንዋመ ፡ ሐኬት ፡ እንቅልፍ ፡ የሚያንቀላፉ ፡ ሰዎች ፡ በእሪት ፡ ሳሉ ፡ ነውና ።
ወእለሂ ፡ ይሰክሩ ፡ ሌሊተ ፡ ይሰክሩ ።
 በኃጢአት ፡ እረቂ ፡ የሚሰክሩ ፡ ሰዎችም ፡ በድንቁርና ፡ ሳሉ ፡ ነውና ።

፰ ፡ ወንሕነሰ ፡ እንዘ ፡ ውሉደ ፡ መዓልት ፡ ንሕነ ፡ ንንቃሕ ። (ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፲፪ ።)
 እኛ ፡ ግን ፡ የዕውቀት ፡ የወንጌል ፡ ልጆች ፡ ነንና ፡ ከንዋመ ፡ ሐኬት ፡ እንንቃ ።
ወንልበስ ፡ ልብሰ ፡ ኀጺን ፡ ዘሃይማኖት ፡ ወዘተፋቅሮ ።
 ልብሰ ፡ ኀጺን ፡ ግሥ ፡ ነው ፡ ሃይማኖትን ፡ ፍቅርን ፡ ገንዘብ ፡ እናድርግ ። አንድም ፡ ሰምና ፡ ወርቅ
 ልብሰ ፡ ኀፂን ፡ ምግባር ፡ ሃይማኖትን ፡ ገንዘብ ፡ እናድርግ ። አንድም ፡ ልብሰ ፡ ኀጺን ፡) ጥሩር ፡ እንልበስ
ዘሃይማኖት ፡ ሲል ፡ ዘውእቱ ፡ ሃይማኖት ።
 ይኸውም ፡ ሃይማኖት ፡ ምግባር ፡ ነው ።
ወንትቀጸል ፡ ጌራ ፡ ተስፋ ፡ መድኃኒት ። (ኢሳ ፡ ፶፱ ፡ ፲፯ ፡ ኤፌ ፡ ፮ ፡ ፲፬ ፡ ፲፯ ።)
 ቦርቦርቴ ፡ እንድፋ ፡ (አለ ፡) ተስፋ ፡ ትንሣኤ ፡ እንያዝ ።

፱ ፡ እስመ ፡ ኢረሰየነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመንሡት ።
 እግዚአብሔር ፡ ጥንቱን ፡ ለሞት ፡ አልፈጠረንምና ።
ዘእንበለ ፡ ለሕይወት ፡ ወለመድኃኒት ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
 በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቃልነት ፡ ለሕይወት ፡ ፈጥሮናል ፡ እንጂ ፡ ኢረሰየነ ፡ ለመንሡት
 ዘሞተ ፡ ለነ ፡ ማንሻ ።

፲ ፡ ዘሞተ ፡ ለነ ፡ ቤዛነ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፬ ፡ ፰ ፡ ፱ ።)
 ለኛ ፡ ቤዛ ፡ ኾኖ ፡ በሞተ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በዙርነት ፡ እንድንነሣ ፡ አድርጎናል ፡ እንጂ ፡ ፈር
 ሰን ፡ በስብሰን ፡ እንድንቀር ፡ አላደረገንምና ።
እመኒ ፡ ንቁሃን ፡ ንሕነ ።
 ንሕነ ፡ ሕያዋን ፡ እለ ፡ ንተርፍ ፡ ያለንም ፡ ብንኾን ።
ወእመኒ ፡ ንውማን ፡ ምስሌሁ ፡ ንሕዮ ፡ ኵልነ ። (፵ ፡ ፱ ፡ ፲፭ ።)
 ኢንበጽሖሙ ፡ ለምውታን ፡ ያለንም ፡ ብንኾን ፡ ሙታችንም ፡ ቢኾኑ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዶ ፡ ለመኖር ፡ እን
 ደሱ ፡ እንነሣለን ።

ክፍል ፡ ፮ ።

፲፩ ፡ ወይእዜኒ ፡ አስተፍሥሑ ፡ ቢጸክሙ ፡ በእንተዝ ።
 አሁንም ፡ ስለዚህ ፡ ወንድሞቻችሁን ፡ አስተምሩ ። አንድም ፡ ለወንድሞቻችሁ ፡ ይህን ፡ ነግራችሁ ፡
 ደስ ፡ አሰኙ ።
ወይሕንጽ ፡ ፩ ፡ ካልአ ።
 አንዱ ፡ አንዱን ፡ ሕንጻ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያድርግ ።
ዘከመ ፡ ትገብሩ ፡ ዓዲ ፡ (ዕብ ፡ ፲ ፡ ፳፬ ፡ ፳፭ ።)
 እናንተ ፡ እንደምትሠሩ ። አንድም ፡ (ዓዲ ፡ ይሕንጽ ፡ ካልአ ፡) ዳግመኛ ፡ አንዱ ፡ አንዱን ፡ ሕንጻ ፡ እግ
 ዚአብሔር ፡ ያድርግ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፪ ፡ ወናስተበቍዓክሙ ፡ እኃዊነ ፡ ዑቅምሙ ፡ ለእለ ፡ ይጻምዉ ፡ በውስቴትክሙ ፡ (፩፡ ቆሮ፡ ፲፮፡ ፲፰ ።)
ወንድሞቻችን ፡ እናንተን ፡ በማስተማር ፡ የሚደክሙ ፡ መምህራንን ፡ ዘመድ ፡ ዘመድ ፡ በሏቸው ፡
ብለን ፡ እንማልዳችኋለን ።
ወለእለ ፡ ይቀውሙ ፡ ለክሙ ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ወይሜህሩክሙ ።
ጸንተው ፡ የጌታችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ነገር ፡ የሚያስተምሩ ፡ መምህራንን ፡ ዘመድ ፡ ዘመድ
በሏቸው ።

፲፫ ፡ አክብርዎሙ ፡ ፈድፋደ ።
እርዷቸው ።
ወአፍቅርዎሙ ፡ በእንተ ፡ ምግባሮሙ ።
በበጎ ፡ ሥራቸውም ፡ ምስሏቸው ።
ወተእምኀዎሙ ።
እክብሯቸው ።
ወናስተበቍዓክሙ ፡ እኃዊነ ፡ ገሥጽዎሙ ፡ ለዘሉፋን ።
መስከ ፡ እሾችን ፡ ገሥጿቸው ፡ ብለን ፡ እንማልዳችኋለን ፡ ተግሣጹ ፡ እንደ ፡ እንጀራ ፡ በ በሉ ፡ ግማሽ
ግማሽ ፡ ቢበሉ ፡ ኩርማን ፡ መስጠት ፡ ነው ።
ናዝዝዎሙ ፡ ለኀዙናን ።
ኀዙናንን ፡ ደስ ፡ አሰኙዋቸው ።
ጹርዎሙ ፡ ለድኩማን (፪፡ ተሰ፡ ፫፡ ፲፭ ።)
ድኩማንን ፡ እጽኗቸው ።
ወተዓገሡ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ።
ኹሉን ፡ ታገሡ ።

፲፭ ፡ ዑቁ ፡ ኢትግብሩ ፡ እኩየ ፡ ህየንተ ፡ እኪት ፡ (ምሳ፡ ፳፡ ፳፪፡ ሮሜ፡ ፲፪፡ ፲፯፡ ፩፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፱ ።)
የበደላችሁን ፡ እንደበደለን ፡ እንበድለው ፡ አትበሉ ፡ እንዲትሉ ፡ ዕወቁ ።
እላ ፡ ተባደሩ ፡ በሠናይ ፡ ለሠናይ ፡ በበይናቲክሙ ።
እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ለበጎው ፡ ነገር ፡ ተቀዳደሙ ፡ እንጂ ።
ወለኵሉሂ ።
በበይናቲክሙ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ለሌላውም ፡ ኹሉ ፡ በበጎ ፡ ነገር ፡ ተቀዳደሙ ፡ እንጂ ።

፲፮ ፡ ተፈሥሑ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ (ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፳ ።)
ኹልጊዜ ፡ በሥራችሁ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ።
ወጸልዩ ፡ ወትረ ። (ሉቃ፡ ፲፰፡ ፩ ፡ ሮሜ፡ ፲፪፡ ፲፪፡ ቈላ፡ ፬፡ ፪ ።)
ሁልጊዜ ፡ ጸልዩ ።
፲፯ ፡ እዕኵትዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ (ኤፌ፡ ፭ ፡ ፳ ፡ ቈላ ፡ ፪ ፡ ፯ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ።)
ስለተደረገላችሁ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ።
፲፰ ፡ እስመ ፡ ዝውእቱ ፡ ፈቃዱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንቲአክሙ ።
ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሻው ፡ ይህ ፡ ነውና ፡ (እሉ) ፡ መመስገን ፡ ነውና ።
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
(እዕኩትዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እብ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡) በኢየሱስ ፡ ክር
ስቶስ ፡ በለተደረገላችሁ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ።

፲፱ ፡ መንፈስ ፡ ኢታጥፍኡ ፡ (፩፡ ቆሮ፡ ፲፬፡ ፴፡ ፴፱ ።)
ልቡናችሁን ፡ አታባክኑ ።

፳ ፡ ወተነብዮ ፡ ኢትመንኑ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፬ ፡ ፩ ።)
ትርጓሜ ፡ አትናቁ ፡ እንድም ፡ (መንፈስ ፡ ኢታጥፍኡ ፡) እድሮባችሁ ፡ ያለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ የማ
ይገባ ፡ ሥራ ፡ ሠርታችሁ ፡ እንዲለያችሁ ፡ አታድርጉ ።
ወተነብዮ ፡ ኢትመንኑ ።
መጻሕፍትን ፡ ዐውቆ ፡ መናገርንም ፡ አትናቁ ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፩ ፡ ወኵሎ ፡ አመክሩ ።
ኹሉንም ፡ መርምሩ ።
ወዘሠናየ ፡ አጽንዑ ፡ (ሮሜ፡ ፱፡ ፲፫፡ ፩፡ ዮሐ፡ ፬፡ ፩ ።)
የከፋውን ፡ ትታችሁ ፡ የበጎውን ፡ ያዙ ።

፳፪ ፡ ወተገኃሡ ፡ እምኵሉ ፡ ምግባር ፡ እኩይ ።
ከከፋው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ተለዩ ።

፳፫ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ እምላከ ፡ ሰላም ፡ ይቀድስክሙ ፡ ፍጹመ ፡ (ሮሚ ፡፲፭ ፡፴፫ ።)
የፍቅር ፡ የአንድነት ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔር ፡ በፍጹም ፡ ክብር ፡ ያክብራችሁ ።
ወያጥዒክሙ ፡ ነፍስክሙ ፡ ወመንፈስክሙ ፡ ወሥጋክሙ ።
በሥጋ ፡ በነፍስ ፡ በደመ ፡ ነፍስ ፡ሕያዋን ፡ ያደርጋችሁ ።
በንጽሕ ፡ እስከ ፡ ምጽአተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
(ይቀድስክሙ ፡ በንጽሕ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡) ጌታችን ፡ እስከሚመጣበት ፡እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡ በን ጽሕና ፡ እንድትጸኑ ፡ ያድርጋችሁ ።

፳፬ ፡ ወዘጸውዐክሙ ፡ ጻድቅ ፡ ውእቱ ፡ ይግበር ፡ ለክሙ ። (፩፡ ቆሮ፡ ፩፡ ፱ ፲ ፲፫፡ ፱፡ ተሰ፡ ፫፡ ፫፡ ፱፡ ጢሞ፡ ፱፡ ፲፫።)
በሃይማኖት ፡ የጠራችሁ ፡ እርሱ ፡ ቸር ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነውና ፡ ይግበር ፡ ለክሙ ፡ ይህን ፡ ያደርግላችሁ ፡ እንድም ፡ ይህን ፡ ያደርግላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ቸር ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ።

፳፭ ፡ አኃዊነ ፡ ጸልዩ ፡ ለነ ።
ወንድሞቻችን ፡ ጸልዩልን ።

፳፮ ፡ አምኁ ፡ ኵሎ ፡ አኃዊነ ፡ በአምኃ ፡ ቅድሳት ። (ሮሜ ፡፲፮ ፡፲፮ ።)
ከኤሳው ፡ ከይሁዳ ፡ ከዲያብሎስ ፡ በተለየ ፡ ሰላምታ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ኹሉ ፡ ቸር ፡ እላችሁን ፡ በሉ።

፳፯ ፡ አምሕለክሙ ፡ በእግዚእነ ፡ ታንብብዋ ፡ ለዛቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ አኃዊነ ፡ ቅዱሳን ።
ይህችን ፡ ከታብ ፡ ለምእመናን ፡ በጉባኤ ፡ ታስነቧት ፡ ዘንድ ፡ አማጸናችኋለች ።ከግዝት መሐላ ይቀላል ፡ ብሎ ፡ አምሕለክሙ ፡ አለ ፡ ከግዝትም ፡ መሐላ ፡ እንዲቀል ፡ በዚህ ፡ ይታወቃል ።

፳፰ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምስሌክሙ ።(ሮሜ፡ ፲፮፡ ፳፬፡ ፊል፡ ፬፡ ፳፫ ።)
የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋው ፡ አድሮባችሁ ፡ ይኑር ።
አሜን ።(ሮሜ፡ ፲፮፡ ፳፡ ፳፬፡ ፊል፡ ፬፡ ፳፫ ።)
በውነት ።

ተፈጸመ ፡ መልእክት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ ተሰሎንቄ ፡ ወተጽሕፈ ፡ በአቴና ፡
ወተፈነወ ፡ ምስለ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ወስልዋኖስ ።

በአቴና ፡ የተጻፈ ፡ በጢሞቴዎስና ፡ በስልዋኖስ ፡ እጅ ፡ ከጳውሎስ ፡ በተሰሎንቄ ፡ ላሉ ፡ ሰዎች ፡ የተላከ ፡ ክታብ ፡ ደረሰ ፡ ተፈጸመ ።
ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ።
እነግሥት ፡ ላስጀመረን ፡ አስጀምሮ ፡ ላስጨረሰን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

www.ethiopianorthodox.org